Alemnew Hulgizie:

ቍ ልደተ እግዚእ - ክፍል ፩ ቍ

<ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳስተማረው>

ከበዓላት ኹሉ ይልቅ እጅግ የተከበረውና የተወደደው በዓል እየደረሰ ነው። አንድ ሰው ይህን በዓል “ርእሰ በዓላት” ብሎ ቢጠራው ልክ ነው። ለምን? ወልደ እግዚአብሔር በሥጋ የተወለደበት ዕፁብ ድንቅ በዓል ነውና።

ይህ በዓል ለበዓለ ጥምቀት፣ ለበዓለ ትንሣኤ፣ ለበዓለ እርገትና ለበዓለ ኃምሳ ጥንታቸውና ምክንያታቸው ነው። ጌታችን በሥጋ ባይወለድ ኖሮ፥ ባልተጠመቀ ብሎም በዓለ ጥምቀት ባልነበረ ነበርና። የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ባይኾን ኖሮ፥ ባልተሰቀለ ብሎም በዓለ ትንሣኤ ባልነበረ ነበርና። አዋን አምላክ ሰው ባይኾን ኖሮ፥ መንፈስ ቅዱስን ባልላከ ብሎም በዓለ ኃምሳ ባልነበረ ነበርና። ስለዚህ ውኖች ከአንድ ምንጭ ፈልቀው በተለያየ ወንዝ እንደሚፈስሱ ኹሉ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው በዓላትም መነሻቸው በዓለ ልደት ነው።

ይህ በዓል ከሌሎች በዓላት ይልቅ ለየት የሚያደርገው ግን ለሌሎች በዓላት ጥንት በመኾኑ ብቻ አይደለም፤ በሌሎች በዓላት ከተደረጉት ምሥጢራት ይልቅ በዚህ ዕለት የተደረገው ምሥጢር ይበልጥ ዕፁብ ድንቅ ስለ ኾነም ጭምር ነው እንጂ። ይህንንም የምለው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም እንኳን ነውር የሌለበት ንጹሃ ባሕርይ ቢኾንም በመልዕልተ መስቀል ላይ ተቀሰቅሎ የሞተው አስቀድሞ በዚህ ዕለት መዋቲ ሥጋን ነሥቶ ስለ ተዋሐደ ነው። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ቢኾንም ሰው ለመኾን ፈቃዱ ኾኗልና፣ የሰው ልብም መርምሮ ሊደርስበት የማይችለውን ትሕትና አሳይቷልና መንክር ነው። እጅግ የሚያስደንቀውና ፍጹም የማይደረስበት ይህ ነውና። ንዑድ ክቡር የሚኾን ጳውሎስም በመደነቅ እንዲህ አለ፦ “የዚህ የመልካም አምልኮ ምሥጢር ታላቅ ነው” (1ኛ ጢሞ.3፡16)። ታላቅ የኾነውስ ለምንድን ነው? “እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠ ነውና” (1ኛ ጢሞ.3፡16)። ዳግመኛም በሌላ ሥፍራ እንዲህ አለ፦ “የነሣውን ከአብርሃም ዘር እንጂ ከመላእክት የነሣው አይደለምና። ስለዚህም በነገር ኹሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው” (ዕብ.2፡16-17)።

በመኾኑም ከሌሎች በዓላት ይልቅ ይህን በዓል እጅግ እወደዋለሁ። እናንተም ከእኔ ጋራ ይህን በዓል እጅግ ትወዱትና ታከብሩት ዘንድ እሻለሁ። ስለዚህ እማፀናችኋለሁ፤ እማልዳችኋለሁም! በታላቅ ንቃትና ትጋት ኾናችሁ ወደ ቤተ ክርስቲያን ኑ! አንድ ሰውስ እንኳ ከቤተ ክርስቲያን ቀርቶ በቤቱ እንዳያድር! አዎን ኑና ጌታችን በበረት ተኝቶ እንየው፤ ኑና ያ ከሕሊናት የሚርቀውና አስደናቂው ብርሃን በጨርቅ ተጠቅልሎ እንመልከተው።

ወዮ! እርሱ እንኳን ልዑለ ባሕርይ ኾኖ ሳለ ስለ እኔና ስለ እናንተ ብሎ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በበረት ለመተኛት ያላፈረብን፥ እኛ ግን ቤታችንን እንኳን ትተን ወደ እርሱ ለመምጣት የማንፈቅድ ከኾነ ሊደረግልን የሚችለው ይቅርታ እንደ ምን ያለ ይቅርታ ነው? እኮ ሰብአ ሰገል - አዎን እነዚያ አረማውያንና የባዕድ አገር ሰዎች - ከፋርስ ተነሥተው በበረት የተኛውን ጌታ ለማየት መጥተው እያለ፥ እኛ ክርስቲያኖች ግን ይህን በረከት ለማየት ከቤታችን ተነሥተን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣት የምንነጫነጭና የምንቸገር ከኾነ ሊደረግልን የሚችለው ቸርነት እንደ ምን ያለ ቸርነት ነው? እኔ ግን እላለሁ! እንዲህ የምንነጫነጨውና የምንቸገረው እምነተ ጎዶሎዎች ስለ ኾንን ነው። እምነት’ማ ቢኖረን ልክ ሰብአ ሰገል በበረት ተኝቶ ሳለ ለማየት እንደ መጡ፥ እኛም እርሱን ለማየት እዚህ በመጣን ነበር። ያኔ በበረቱ እንደ ተኛ አሁንም በዚህ መሠዊያ ላይ አለና።

ተ ልደተ እግዚእ - ፪

በእርግጥ በዚህ በመሠዊያው ላይ ያለው የጌታችን ሥጋ እንደ ቀድሞ በጨርቅ የተጠቀለለ አይደለም፤ ፍጹም በመንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ። እንደዚህ ብዬ ስናገር ምን ማለቴ እንደ ኾነም በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙት ይረዱታል። ሰብአ ሰገል ወደ ጌታችን መጥተው ሰገዱለት፤ እናንተ ሕሊናችሁን ንጹህ አድርጋችሁ ከመጣችሁ ግን እርሱን

እንድትበሉትና ይዛችሁትም ወደ ቤታችሁ ትኼዱ ዘንድ እንፈቅድላችኋለን። ስለዚህ መባችሁን ይዛችሁ ቅረቡ - ነገር ግን ሰብአ ሰገል ይዘዉት እንደ መጡት መባ አይደለም፤ ከእነዚህ ይልቅ ልዑልና ቅዱስ የኾነ መባን ነው እንጂ። ሰብአ ሰገል ወርቅ ይዘው መጡ፤ እናንተ ግን በወርቅ ፈንታ በመጠን መኖርንና ንጹህ ምግባርን ይዛችሁ ኑ! ሰብአ ሰገል ዕጣን ይዘው መጡ፤ እናንተ ግን ነውር የሌለበት ንጹህ ጸሎትን ከመንፈሳዊ ዕጣን ጋር ይዛችሁ ኑ! ሰብአ ሰገል ከርቤ ይዘው መጡ፤ እናንተ ግን ትሕትናንና የተዋረደ ልብን ፍቅርንም ይዛችሁ ኑ! እነዚህን መባዎች ይዛችሁ ከመጣችሁ ከዚህ ቅዱስ ማዕድ (ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ) ያለ ዕዳ መሳተፍ ይቻላችኋል።

እንደዚህ ብዬ የምነግራችሁም በዚያች ሌሊት ብዙዎቻችሁ ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ ለመሳተፍ እንደምትመጡ ስለማውቅ ነው። ስለዚህ አሁን እንደዚህ ብዬ መናገሬ ለድኅነት ያይደለ ለዕዳ ለፍዳ እንዳይኾንብን ነው። አዎን እንደዚህ ብዬ የምነግራችሁ - የምማጠናችሁ ወደ ቅዱስ ቁርባን ስትቀርቡ አስቀድማችሁ ልቡናችሁን ከርኩስ አሳብ ኹሉ ንጹህ እንድታደርጉ ስለምሻ ነው።

እማልዳችኋለሁ! ከእናንተ መካከል አንድ ሰውስ እንኳ “እኔ በደሌን ሳስበው ያሳፍረኛል፤ ሕሊናዬ በብዙ ኃጢአት የተሞላ ነው። ከባድ ሸክምም አለብኝ” አይበለኝ። እናንተ ፈቃደኞች ከኾናችሁ ከአሁኗ ሰዓት ጀምራችሁ [ንስሐ ብትገቡና] ራሳችሁን ብትገዙ፣ ብትጸልዩ፣ ትግሃ ሌሊትንም ብታበዙ የሚቀጥሉት አምስት ቀናት የኃጢአት ቡትቶአችሁን አሽቀንጥራችሁ ለመጣል በቂ ናቸው። የጊዜው ማጠር አትመልከቱ፤ የእግዚአብሔርን ቸርነት አስቡ እንጂ። አታስታውሱም? የነነዌ ሰዎች የእግዚአብሔር ቊጣ እንዲመለስ ያደረጉት በሦስት ቀናት ውስጥ ነበር። የጊዜው ማጠር ይህን ለማድረግ ዕንቅፋት አልኾነባቸውም። የልቡናቸው መመለስ እግዚአብሔርም ሊያደርግባቸው ከተናገረው ክፉ ነገር እንዲጸጸት አድርገውታል (ዮና.3)። ዘማይቱ ሴትም በሸርፍራፊ ጊዜ ውስጥ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥታ በደሏ ኹሉ ተሠርዮላታል (ሉቃ.7)። በዚህ ጊዜ አይሁድ፥ ሴቷ ማን እንደ ኾነች ቢያውቅ ኖሮ እንድትዳስሰው ባላደረገ ነበር ብለው አምተውታል። ጌታችን ግን ዘማይቱ ወደ እርሱ እንድትቀርብ በማድረግ እነርሱን ዝም አሰኝቷቸዋል፤ የሴቲቱንም ትጋት አመስግኖ ኃጢአቷን ኹሉ ይቅር ብሎ ሰደዳት። የዚህ መልእክቱስ ምንድን ነው? ሴቲቱ የመጣችው ትጉህ ሕሊናን ይዛ ነው፤ የመጣችው ሥርየተ ኃጢአትን ሽቶ በሚንበለበል ልብ ነው፤ አዎን ሴቲቱ ወደ ጌታችን የቀረበችው በደሏን ይቅር እንደሚላት ጽኑዕ እምነትን ገንዘብ አድርጋ ነው። ያን ጊዜ የተቀደሰ እግሩን ዳሰሰች። አለቀሰች። እንባዋን አፈሰሰች። እግሩን አራሰች። በራስ ፀጉሯም እግሩን አበሰች። እግሩን ሳመችው። ሽቱም ቀባችው።

ወንዶችን ለዝሙት ትማርክበት የነበረው መንገድ የንስሐ መድኃኒትን አዘጋጀችበት። ለሴሰኝነት ታይበት የነበረው ዓይኗ አሁን የንስሐ እንባ ያፈሰሱ ዘንድ ተጠቀመችበት። ብዙዎችን በበደል ዓዘቅት ይወድቁ ዘንድ ያጠመደችበት ፀጉሯ አሁን የጌታችንን እግር አበሰችበት። ዘማውያንን የማረከችበት ሽቶ አሁን የጌታችንን እግር ቀባችበት።

እናንተም እንደዚህ አድርጉ። አዎ! እናንተም እግዚአብሔርን ባሳዘናችሁበት መንገድ መቅረቢያችሁ አድርጉት። በስርቆት እግዚአብሔርን አሳዝናችሁታልን? ያለ አግባብ የወሰዳችሁትን ገንዘብ ለባለቤቱ መልሱ። ጨምራችሁም ስጡ። ከዘኪዎስ ጋር ኾናችሁም፦ “ሰርቄ እንደ ኾነ አራት ዕጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ” በሉ (ሉቃ.19፡8)። በአንደበታችሁ ብዙ ሰዎችን በማንጓጠጥና በመስደብ ፈጣሪያችሁን አሳዝናችሁታልን? ንጹህ ጸሎትን በመጸለይ፣ የሚረግሙአችሁን በመመረቅ፣ የሚበድሉአችሁንም በማመስገን በዚሁ አንደበታችሁ ተማፀኑት።

እነዚህን ለማድረግ ብዙ ቀናትን አይሹም። እነዚህን ነገሮች ለማከናወን ብዙ ዓመታትን አይጠይቁም። እነዚህን ለማድረግ ከእናንተ የሚፈለገው በጎ ፈቃደኝነታችሁ ብቻ ነው፤ ይህን ስታደርጉም በአንድ ቀን ውስጥ እነዚህን ማከናወን ትችላላችሁ። ከክፋት ራቁ። በጎ ምግባርን ያዙ። ከእንግዲህ ወዲህ እነዚህን ኃጢአቶች ላለማድረግ ወስኑ። ይህን ካደረጋችሁም ወደ ምሥጢር መቅረብ ትችላላችሁ። ዕዳ በደልም አይኾንባችሁም። ከቀድሞ ክፉ መንገዳችን ብንመለስ፣ መልሰን ወደዚያ ኃጢአት ላለመውደቅም ብንወስን፥ እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ከእኛ ምንም ነገር እንደማይሻ እውነት ያለ ሐሰት እነግራችኋለሁ። ይህንንም የምለው አምላካችን መሐሪና ቸር ስለ ኾነ ነው። እርጉዝ ሴት ለመውለድ እንድምትቸኩል ኹሉ እግዚአብሔርም ሰውን ለመማር ይቸኩላል - ይህ እንዳይኾን የሚከለክለው ኃጢአታችን ነው።

ስለዚህ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ኾኖ እንዳንተያይ የከለከለንን የበደላችንን አጥር እናፍርስ። በእነዚህ አምስት

ቀናት ውስጥም ይህን ኹሉ በመተውና ሱባኤ በመያዝ ገና ከአሁኑ በዓሉን ማክበር እንጀምር።

ተ ልደተ እግዚእነ - ፫ ተ

“ፍርድቤቶች፥ ምክር ቤቶችም ሆይ! ደኅና ሰንብቱ። የዕለት ለዕለት ሥራዬ ሆይ! ከእነ ውጣ ውረድህ ደኅና ሰንብት። በሚቀጥሉት ቀናት ውስጥ ነፍሴን ላድናት ቆርጫለሁና። ‘ሰው ዓለሙን ኹሉ ቢያተርፍ፥ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋልና?’ (ማቴ.16፡26)።” አዎን! ለሚቀጥሉት ቀናት እንዲህ እናድርግ!

ሰብአ ሰገል ከፋርስ አገር መጡ። እኛም ከዚህ ዓለም ጫጫታ ወጥተን ወደ ንጉሥ ክርስቶስ እንምጣ! እኛ ከፈቀድን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ሩቅ አይደለምና። እንዴት? ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ባሕር ማቋረጥ አያሻንምና፤ ወደ አምላካችን ለመምጣት ወደ ተራሮች አፋፍ መውጣት አያስፈልገንምና።

ታዲያ ምንድን ነው የሚያስፈልገን?። ቤታችንን እንዝጋ፤ በደላችንን አስበን እናንባ - አብዝተንም እናልቅስ። ያን ጊዜ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የቆመው ግድግዳ ይደረማመሳል። ያን ጊዜ ወደ አምላካችን እንዳንቀርብ የከለከለን ዕንቅፋቱ ይወገዳል። አዎን ያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ሩቅ ኾኖብን የነበረው መንገድ ቅርብ ይኾናል። “አምላክ ቅሩብ አነ እግዚአብሔር ወኢኮንኩ አምላከ ርኁቀ - [ስንለምንህ ባትሰማን ብትርቀን ነው ትሉኝ እንደኾነ] እኔስ በእውነት [ለለመነኝ ሰው] ቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ ሩቅ አምላክ አይደለሁም” ይላልና እግዚአብሔር (ኤር.23፡23)። ዳግመኛም ክቡር ዳዊት እንዲህ ብሏልና፡- “ቅሩብ እግዚአብሔር ለኵሎሙ እለ ይጼውዕዎ - እግዚአብሔር ለሚለምኑት ኹሉ ቅርብ ነው” (መዝ.145፡18)።

ልደተ እግዚእነ -፬

ብዙ ሰዎች ግን ምንም እንኳን እጅግ በዕውቀት ሕፃናትና ደንታቢሶች፣ ስፍር ቊጥር በሌለው ክፋትም የተሞሉ ቢኾኑም ቅሉ፥ ምንም ሳይዘጋጁ መቅረባቸው እንደ ምን ያለ ዕዳ - እንደ ምን ያለ በደልም እንደሚኾንባቸው አያስተውሉም። ይህን ሳያስተውሉም እንዲሁ እንደ ተራ ኅብስትና መጠጥ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል ይጣደፋሉ። ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል የሚያስፈልገው ንጹህ ልብስ ሳይኾን ንጹህና የተዋረደ ልብ መኾኑን ሳያውቁ ይቀርባሉ።

ንጹህና በሕሊናው ርኵስ አሳብ የሌለበት ሰው በየዕለቱ ከምሥጢሩ መሳተፍ ይችላል። በኃጢአት የተተበተበ ሰው ግን አስቀድሞ ንስሐ ሳይገባ ከዚህ ምሥጢር ሊሳተፍ አይገባውም። ደሙ “ስቴ ዘመኰንን - የሚፈርድ መጠጥ” ነውና፥ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ፥ ይህቺውንም በንስሐ ሳይታጠብና ሳይገባ’ው ወደዚህ መቅረቡ በበደል ላይ ሌላ በደል ከመጨመር ውጭ ምንም የሚያስገኝለት በቁሜት የለም።

ለዚህም ነው፥ እንዲሁ ደንታቢሶችና አፍአዊ ዝግጅት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጋችሁ ወደዚህ መለኮታዊ ምሥጢር እንዳትቀርቡ የምለምናችሁ! አዎን ለዚህ ነው፥ ከዚህ ቅዱስ ምሥጢር መሳተፍ ስትፈልጉ አስቀድማችሁ ንስሐ እንድትገቡ፣ ስንፍናችሁን ላለመድገምና እንደ ውሻ ወደ ትፋታችሁ እንዳትመለሱ በንስሐና በጸሎት ምጽዋትን በመስጠትና በመንፈሳዊ ተግባራት ኹሉ በመትጋት ለብዙ ቀናት ራሳችሁን እንድታዘጋጁ የምማጠናችሁ! (ምሳ.26፡11)፡

በዓሉን አፍአዊ በኾነ መልኩ ለማክበር ከብዙ ጊዜ በፊት አዲስ ልብስና አዲስ ጫማ ትገዛላችሁ። ብዙ መብልና ብዙ መጠጥ ታዘጋጃላችሁ። ሌላ ለዕለቱ የሚያስፈልጋችሁ ነገርም አስቀድማችሁ ታሰናዳላችሁ። ገላችሁን ትታጠባላችሁ። በሌላ መልኩ ደግሞ ስለ ነፍሳችሁ ምንም ደንታ የሌላችሁ፣ በርኵሰት የቆሸሻችሁ፣ ቃለ እግዚአብሔርን የተራባችሁና የተጠማችሁ ኾናችሁ ማየት በእውነት ያለ ሐሰት እጅግ የሚያበሳጭ ነው።

ለምንድን ነው እንደዚህ የምታደርጉት? ለምንድን ነው ነፍሳችሁ ዕራቆቷ ሳለች፥ አፍአዊ ሰውነታችሁን ብቻ ንጹህ ልብስን የምታለብሱት? ለምንድን ነው ባልንጀራችሁ ለሚያየው ልብስ እጅግ የምትጨነቁ ኾናችሁ ሳለ፥ እግዚአብሔር ለሚያየው ልብስ ግን ግድየለሾች የምትኾኑት?

እስኪ ንገሩኝ! ይህ ምሥጢር መንፈሳዊ እሳት እንደ ኾነ አታውቁምን? ምንጭ፥ ውኖች በኃይል ከምድር ፈልቀው እንዲጎርፉ እንደሚያደርግ፥ ይህ ምሥጢርስ መለኮታዊ እሳት እንደ ኾነ አታውቁምን? ስለዚህ እማልዳችኋለሁ! ገለባ፣ ወይም ዕንጨት ወይም ደረቅ ሣር ከተሸከማችሁ ወደዚህ ምሥጢር አትቅረቡ - ኃጢአታችሁ ሳይኾን እናንተ ራሳችሁ ትቃጠላላችሁና።

✞ ልደተ እግዚእነ - የመጨረሻው ክፍል ✞

ዕንቊ፣ ወርቅና ነሐስ የተሸከማችሁ ከኾነ ቅረቡ። እነዚህ እንደ ገለባው፣ ወይም እንደ ዕንጨቱ፣ ወይም እንደ ደረቅ ሣሩ የሚቃጠሉ ሳይኾኑ ይበልጥ ጽሩያን፣ ንጹሃን የሚኾኑ ናቸውና። ስለዚህ ዕጥፍ ድርብ በቁዔትን ይዛችሁ ወደ ቤታችሁ ትመለሱ ዘንድ ዕንቊንና ወርቅን ነሐስንም የያዛችሁ እንደ ኾነ ወደ ምሥጢር ቅረቡ።

ጥቂትም ቢኾን ክፉ ነገር አግኝቷችሁ ከኾነ ግን አስቀድማችሁ ይህን ከእናንተ አርቁት - አዎን ይህን ከነፍሳችሁ አስወግዱት። የተጣላችሁት ሰው ካለ ታረቁ። የተበደላችሁ ካላችሁ የበደላችሁን ሰው ይቅር በሉት። ቂም በቀላችሁን አስወግዱት። በውስጣችሁ የተፈጠረውን በጎ ያልኾነውንና ያበጠውን አሳብ በይቅርታ ምላጭ በጥታችሁ ሻሩት። ምንም ዓይነት ሁከት በልቡናችሁ አይኑር።

እንደዚህ ብዬ የምነግራችሁም በዚህ ምሥጢር የምትቀበሉት፥ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ክርስቶስን ስለኾነ ነው። ንጉሥ ደግሞ ሰላም የሰፈነበት፣ ፀጥታ የተሞላበትና የተረጋጋ ሊያድር ይገባዋል። ስለዚህ ንጉሥ ክርስቶስን የሚቀበለው ኹለንተናችሁ እንደዚህ ይኹን።

አንተ ሰው እስኪ ንገረኝ! በራስህ ላይ ብዙ ጉዳትን የምታከማቸው ለምንድን ነው? አንድ ሰው የቱንም ያህል ጉዳት ቢያደርስብህም እንኳን፥ አንተ በራስህ ላይ የምታደርሰውን ጉዳት ያህል እርሱ በአንተ ላይ ጉዳት እንደማያደርስ አታውቅምን? "እንዴት?" ብለህ ትጠይቀኝ ይኾናል። እኔም እንዲህ ብዬ እመልስልሃለሁ፦ "ጉዳት ካደረሰብህ ሰው ጋር ባለመታረቅህ ሕገ እግዚአብሔርን ከእግርህ በታች ረግጠሃልና።"

ጠላትህ ሰደበህን? ታዲያ እስኪ ንገረኝ! እግዚአብሔርን የምትሰድበው በዚህ ምክንያት ነውን? ከጠላትህ ጋር አለመታረቅ ማለት ጠላትህን መበቀል ማለት ሳይኾን ታረቁ ብሎ ሕግን የሰጠ እግዚአብሔርን መስደብ ነዋ!

ስለዚህ በዚህ አመካኝተህ ባልንጀራህን አትናቀው፤ ያደረሰብህን በደልንም አግንነህ አትመልከተው። ከዚህ ይልቅ በሕሊናህ እግዚአብሔርንና ፈሪሐ እግዚአብሔርን ስታስብ የሚከተለውን ነገር ልብ በለው። የትኛውን? ስፍር ቁጥር የሌለው በደል ደርሶብህ ሊኾን ይችላል። ውስጥህ ብዙ ተጎድቶ ሊኾን ይችላል። አንተ ግን ራስህን ጨክነህ ከዚህ አውጣው። አውጣውና ጎዳኝ ከምትለው ሰው ጋር ታረቅ። ይህን ስታደርግም ይህ እንዲደረግ ባዘዘው በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ የኾነ ባለሟልነትን ታገኛለህ። ታላቅ የኾነ ክብር ትጎናጸፋለህ። አንተ ትእዛዙን በመተግበር እግዚአብሔርን በዚህ በምድር አክብረኸዋልና፥ እርሱም በሰማያት በታላቅ ክብር ይቀበልሃል። አንተ አሁን ላሳያሃት ጥቂቷን እርሱም በሰማያት እልፍ ዕጥፍ አድርጎ ይከፍልሃል። ስለዚህ ይህን ከማድረግ ቸል አትበል።

እኛ ሥራ ሠርተን አንበቃምና፥ ከባሕርይ አባ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በክብር፣ በጌትነት፣ በሥልጣንና በምልክና አንድ የሚኾን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቸርነቱና ሰውን በመውደዱ ርስቱን መንግሥቱን እንድንወርስ ይርዳን። ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር